# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ቁጥር 190 ታህሳስ 26 2004 ገጽ 1


ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ "በሴቶች ላይ የሚደርሰው ግፍ በሰብዓዊ መብቶች ላይ የሚደርስ ግፍ አካል ነው" ብሎ አድበስብሶ አያልፍም። በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት የሰብዓዊ መብቶች መረገጥ ማነኛው ማሳያ ነው። ይህን ጥቃት መታገል የሴቶች ወይም የወንዶች ኃላፊነት ሳይሆን የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

በተጨማሪም ሴቶችና ወንዶች በጋራ ካልታገልን በስተቀር ትግላችንን ፈቀቅ ማድረግ እንደማንችል ግንቦት 7 ያምናል። ስለሆነም "እህቶችና እናቶች በትግላችን በንቃት ተሳተፉ፤ አብረን ታግለን ነፃነታችንን እናረጋግጥ፤ ሁላችን እንደ ዱባይዋ እህታችን 'የመጨረሻ መሮኛል፣ መሮኛል፣ መሮኛል!!!' ብለን ቆርጠን እንነሳ" ይላል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በጀኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው ኦነግ የወሰደውን አቋም በመደገፍ ግንቦት7ና ጥምረት መግለጫ አወጡ

በጄኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ) በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ጥላ ሥር ከሌሎች የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ተባብሮ ለመታገል መወሰኑን ገሃድ ማድረጉን ተከትሎ ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከትናንትና በስቲያ መግለጫ አውጥቶአል።

"የጋራ ትግል የጋራ አገር" በሚል ርዕስ ግንቦት7 ባወጣው በዚህ መግለጫ "በኢትዮጵያ የሰፈነውን ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት አስወግደን በምትኩ የግልና የወል መብቶች የተከበሩባት፤ ፍትህና እኩልነት የሰፈኑባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመፍጠር በምናደርገው ትግል ውስጥ በጀኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው ኦነግ አዎንታዊ የሆነ ወሳኝ እርምጃ መውሰዱ "በጋራ ትግል የጋራ ጠላታችንን አስወግደን፤ የጋራ አገራችንን ተባብረን ለመገንባት ወደ ሚያስችለን ምዕራፍ ሊያሸጋግረን ይችላል የሚል እምነት እንዳለው ገልጾአል።

"የኦሮሞ ነፃነት ግንባር በአንድ ጠንካራ አመራር ሥር ሆኖ የኦሮሞን ህዝብ ጥቅምና መብት ብቻ ሳይሆን የሃገሪቱን ዜጎችና ሕዝቦች በሙሉ መብቶችና ጥቅሞች በጋራ ለማስከበር በሚደረገው ትግል ተሳታፊ ቢሆን ኖሮ ሊገኝ የሚችለውን ሕዝባዊና ሃገራዊ ጥቅም ግዙፍ እንደሚሆን ማንም አይስተውም ነበር" ያለው የግንቦት7 መግለጫ፤ መግለጫ፤ የኦሮሞ ምሁራን በተለይ የፖለቲካ ልሂቃኑና ኦነግ በአንድነትና በአንድ ድምጽ እየተናገሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነት፣ ለፍትህና ለዲሞክራሲ በሚያደርገው የጋራ ትግል የኦሮሞን ሕዝብ ታላቅነት የሚመጥን ሃገራዊ የኃላፊነት ሚና እንዲጫወቱ ግንቦት 7 እና በርካታ ወገኖች ሲያደርጉት የቆዩት ጥረት የተፈለገውን ውጤት በተፈለገው ጊዜ ሊያመጣ አለመቻሉ እንዳላስደሰተው አልሸሸገም። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በኢትዮጵያ የሚገኙ ባንኮች ደንበኞቻቸው ከ200 ሺ ወይም ከ10 ሺ ዶላር በላይ ገንዘብ ሲያስገቡም ሆነ ሲያስወጡ ለብሄራዊ የጸረ ሽብር የመረጃ ማእከል ሪፖርት እንዲያደርጉ ታዘዙ

የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን በፍርሃት ለማሸምቀቅ ተብሎ በዘረኛው መለስ ዜናዊ የተቋቋመው የጸረ ሽብር የመረጃ መእከል የተባለው መሥሪያቤት ለግልና ለመንግስት ባንኮች ባወረደው መመሪያ ማንኛውም ኢትዮጵያዊም ሆነ የውጭ አገር ዜጋ ከ200 ሺ ብር ጀምሮ በባንኮች ለማስቀመጥ ወይም ለማውጣት በሚሄድበት ጊዜ፣ ባንኮች የግለሰቦችን ስምና ማንነት ለብሄራዊ የጸረ ሽብር የፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማእከል ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የጸረ ሽብር ግብረሀይሉ ከህወሃት ቁንጮዎች በተሰጠው ልዩ መመሪያ ይህን ትእዛዝ ያስተላለፈው፣ በአገር ውስጥ የሚደረግን የጸረ ሽብር እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ነው በሚል ምክንያት እንደሆነና መመሪያው ከጥር 1 ጀምሮ ተግባራዊ የሚመሆን ሲሆን፣ መመሪያውን በማይፈጽሙ ባንኮች ላይ እርምጃ ይወሰዳል ተብሎአል።

አገዛዙ ከዚህ ቀደም ባወጣው መመሪያ ከ10 ሺ ዶላር በላይ ለማስቀመጥ ወይም ለማውጣት ወደ ባንኮች የሚሄዱ ግለሰቦችን ማንነት ራሳቸው ባንኮች እንዲያጣሩ ያደርግ ነበር።

ይሁን እንጅ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ሹሞች በአገር ውስጥ ያለው የፖለቲካ አየር አስፈሪ ሁኔታ ውስጥ መግባቱ ከፍተኛ ስጋትና ፍርሃት ውስጥ ስለከተታቸው ህዝባዊ ተቃውሞ ለማስተባበር ተቃዋሚዎች ከአገር ውስጥም ሆነ ከውጪ የሚላኩላቸውን ገንዘብ ሊጠቀሙበት ይችላሉ በሚል ስጋት አንድ ዜጋ በአንድ ጊዜ ወይም በተከታታይ ቀናት ወይም ወራት በድምሩ እስከ 200 ሺ ብር የሚደርስ ገንዘብ ከባንክ ካወጣ ወይም ወደ ባንክ ካስገባ፣ ባንኮች የግለሰቡን ማንነት ለጸረ ሽብር ግብረሀይሉ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወያኔ አኬልዳማ በሚል ርዕስ ያስተላለፈው ድራማ ከተቃዋሚ ፓርቲዎችና ከፕሬሶች ጋር በተገባው እልክ መሆኑን በረከት ስምኦን ለፓርላማ ተናገረ። አብዛኛው ህዝብ-ለኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ዓመታዊ ግብር አልከፍልም ማለቱንም በረከት አልሸሸገም

የወያኔ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ሚኒስትር እና የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ የሆነው በረከት ስምኦን ሰሞኑን ለሕዝብ ተወካዮች ተብየው የካድሬዎች ምክርቤት ሪፖርት ሲያቀርብ እንደተናገረው በሽብርተኝነት ተከሰው ፍርድቤት እየተመላለሱ ካሉ ዜጎች ጋር ንክኪ አላቸው የተባሉ ፓርቲዎችና የተቃዋሚነት ሚና ያላቸው ፕሬሶች፤ መንግስት አለአግባብ እሥር እየፈፀመ መሆኑን በመጥቀስ" ሰዎቹ ነፃ ናቸው" በሚል ብይን መስጠት በመጀመራቸው፤ በኅብረተሰቡ ውስጥ "ሰዎቹ ለምን ታሰሩ?" የሚል ጥያቄ በመፈጠሩ የተነሳ የህዝቡን ጥያቄና ቅሬታ ለማለዘብ ወይም ህዝቡን ለማስረዳት በሚል መንግስት "አኬልዳማን" ለመስራት ተገዶአል።

በረከት ስሞን ለሸንጎው ባቀረበው ሪፖርት በነርሱ የሚመራው መንግሥት ላይ የተካሄደው ዘመቻ "ተጠርጣሪዎቹ ወንጀል ፈፅመዋል ወይም አልፈፀሙም በሚል ብቻም የሚወሰን ሳይሆን፤ መንግስት ሰዎቹን ማሰር የፈለገው; ሰውን ለማስፈራራትና ኅብረተሰቡን ለማሸበር ስለፈለገ ነው የሚል ሰፊ ዘመቻ በመካሄዱ -መንግስት ይህ አለመሆኑን ለማሳዬት አኬልዳማን ለመስራት ተገዷል" ብሎአል።

አያይዞም በአኬልዳማ ፕሮግራም ላይ ብይን እንዳልተሰጠ፣ ብይን የመስጠት ሥራ የፍ/ቤት መሆኑን፣ ይህንኑ ጉዳይም ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ተጠይቆ ማብራሪያ መስጠቱን ተናግሮአል። ይሁንና አለቃው መለስ ዜናዊ በዚያው ፓርላማ ተብየው የካድሬዎች ሸንጎ ፊት ቀርቦ "የታሰሩት በሙሉ ወንጀለኞች ናቸው። ለሁሉም ከበቂ በላይ መረጃ አለን" በማለት በአደባባይ ስለሰጠው ፍርድ አፈቀላጤው በረከት ያለው ነገር የለም።

የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ደርጅት ዋና ዳይሬክተር የሆነው የህወሃት አባል ዘርዓይ አስገዶም በበኩሉ ድርጅቱ አኬልዳማ የተሰኘውን ፕሮግራም ከሰራ በኋላ በተቃዋሚ ፓርቲዎች በኩል ክስ እንደቀረበበትና የክሱ ግልባጭም አገር ውስጥ ለሚገኙ ኤምባሲዎች በሙሉ እንደተደረገ በመግለጽ ይህ ተግባር የአንድ አገር ሉዐላዊነት የሚጥስ ክስ ነው በማለት በወያኔ አፈናና ሰቆቃ ሥር የሚንቀሳቀሱትን ተቃዋሚዎች ሲወነጅል ተስተውሎአል።

በወያኔ ፓርላማ ውስጥ ብቸኛ ተቃዋሚ የሆነው የአንድነት ፓርቲ አመራር አባል ግርማ ሰይፉ በወያኔዎች የቀረበውን ሪፖርትና የፈጠራ ክስ አጣጥለዋል።

"በአኬልዳማ ዘጋቢ ፊልም እገሌ 10 ወይም 15 ዓመት ይቀጣ ባይባልም፤ ስሙ እየተጠራ "አሸባሪ" ተብሏል። "እኔ እዚህ ም/ቤት ውስጥ ቁጭ ብዬ የተናገርኩት ንግግር ምስሌ እዚያ ውስጥ ገብቶ አሸባሪ ናቸው ከተባሉት ጋር ቀርቧል። እኔ እዚህ ቁጭ ያልኩት ለአሸባሪነት አይደለም፤ አንድነት የአሸባሪ ድርጅት አይደለም፤ ይሄ ስም ማጥፋት ነው" ያሉት ግርማ ሰይፉ ይህንኑ ቅሬታቸውን በአድራሻ ለኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት እና ለኢትዮጵያ የብሮድካስት ባለስልጣን እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት በግልባጭ ፓርቲያቸው በደብዳቤ ማሳወቁን ገልጸው ሆኖም የብሮድካስት ባለስልጣን "በድርጅቱ ኤዲቶሪያል ፖሊሲ መሠረት አስተናግዷቸው" ቢልም፤ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሊያስተናግዳቸው አለመቻሉን ገልጸዋል።

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## የገናን በአል ምክንያት በማድረግ የእርድ እንስሳት ዋጋ እንደጨመረ ተዘገበ

የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት እንደዘገበው የገናን በአል ተከትሎ የእርድ እንስሳት ዋጋና በከፍተኛ ደረጃ የጨመረ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ የእርድ ከብት ከ12 ሺ ብር ጀምሮ በመሸጥ ላይ ነው።

በአዲስ አበባ ዶሮ ከ170 እስከ 200 ብር፣ በግ ከ1200 ብር እስከ 1700 ብር፣ ፍየል ከ1000 እስከ 1800 ብር በመሸት ላይ ነው። ቅቤ በኪሎ በአማካኝ 130 ብር ዘይት 24 ብር ፣ አንድ ኪሎ ስጋ ደግሞ 90 ብር እየተሸጠ ነው። ስኳር በኪሎ 14፣ ሽሮ ደግሞ 26 ብር በመሸጥ ላይ ነው።

በድሬዳዋ ደግሞ ፍየል ዝቅተኛው 1200 ብር፣ የበሬ ስጋ 90 ብር፣ ነጭ ሽንኩርት በኪሎ 40 ብር ቀዩ ደግሞ 11 ብር ነው ። ዶሮ 100 ብር፣ ለጋ ቅቤ እስከ 160 ብር እንደሚሄድ የዘገበው የኢሳት ዘጋቢ በርካታ ዜጎች "ኑሮን በጾጋ ከመቀበል ውጭ ሌላ ምንም አማራጭ የለውም፣ አመት በአል የተወሰኑት ሰዎች ነው ሲሉ " አስተያየት እየሰጡ እንደሆነ አረጋግጦአል።

## "የመጨረሻ መሮኛል፣ መሮኛል፣ መሮኛል!!!"
## በኤምሬት የምትገኝ እህታችን የቁጭትና እልህ ለቅሶ

በደረሰባቸው በደል የተቆጡ በአረብ አገራት የሚገኙ እህቶቻችን በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ ምሬታቸውና ቁጭታቸውን እየገለጹ ነው። በቅርቡ በአባይ ግድብ ሰበብ የእነዚህ ምስኪን ኢትዮጵያዊያንን የድካም ውጤት ለመዝረፍ ወደ አረብ ኤምሬት ያመራው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ልዑካን ቡድን ያልጠበቀው የቁጣ ናዳ ወርዶበታል።

የአንድ ሥርዓት ምንነት በገሃድ ከሚገልጹ ነገሮች አንዱ የሴቶች መብት አያያዝ ነው። ለሴቶች ከበሬታ የሌለው፤ ሴቶችን በከፍተኛ ችግር ውስጥ የሚያኖር ሥርዓት፣ ውጫዊ ገጽታው ምንም ይምሰል ምን ግፈኛ ሥርዓት ነው። ለሴቶች የማይመች ሥርዓት ለሰው ልጅ በሙሉ - ማለትም ለወንዶችም ጭምር - የማይመች ሥርዓት ነው።

በዲሞክራሲና በህግ የበላይነት ላይ እንደሚያደርገው ሁሉ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ስለሴቶች መብት እጅግ ብዙ ያወራል። በተግባር ግን አገዛዙ ኢትዮጵያዊያን ሴቶችን መጠቀሚያ እንጂ የራሱ አካል አድርጓ አይቷቸው አያውቅም። በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያዊያን ሴቶች ላይ የሚደርሰው ሰቆቃ ህሊና ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ሆኗል።

በሁሉም የእድሜ ደረጃ ውስጥ ያሉ ሴቶች በአረብ አገራት በቤት ሠራተኝነት ለማገልገል በረሃ ማቋረጥ፤ ባህርን በታንኳ መሻገር የጀመሩት በመለስ ዜናዊ የግፍ አገዛዝ ዘመን ነው። ለቤት ሠራተኝነት በህጋዊ መንገድ ወደ አረብ አገራት ለመሄድ ትዳርን መበተን፤ የራስንና የዘመድን ጥሪት አሟጦ ከአስር ሺህዎች ብር በላይ መክፈል የተጀመረው በመለስ ዜናዊ የግፍ አገዛዝ ዘመን ነው። ወደ ምዕራቡ አገራት በትዳር ስም ለሚወስዳቸው ሰው በመቶ ሺህ የሚገመት ብር መክፈል የተጀመረው በመለስ ዜናዊ የአገዛዝ ዘመን ነው።

በውጭ አገራትም በአገር ውስጥም የእህቶቻችን ለቅሶ በርክቷል። ከፎቅ ተገፍትረው የሚወረወሩ፤ በፈላ ውሃ የሚቀቀሉ፤ አሲድ የሚረጭባቸው፤ የአሳዳሪዎቻቸው ፍላጎት ማርኪያ የሆኑ እህቶቻችን ሰቆቃ እንቅልፍ ይነሳናል። በዚህ ሁኔታ ያሉ እህቶቻችን የወያኔ ኩባንያዎች ሃብት ማጋበሻ መሆናቸው ያንገበግበናል።

የኢትዮጵያ ሴቶች ክብር መደፈር የአገራችን እና የሁላችንም ክብር መደፈር ዓይነተኛ መገለጫ ነው።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሀገራቸውን ሲዖል አድርጎ፣ በየባዕድ ሃገሩ በአስከፊ ሁኔታ ለመኖር እንዲገደዱ ከአደረገ በኋላ፣ በራሱ ኩባንያዎች በቪዛ፣ በተለያዩ ሰነዶች እና በደላላነት በየወሩ በብዙ ሚሊዮን የሚገመት ሃብት የሚያጋብሰው አንሶት፣ አይኑን በጨው አጥቦ በአባይ ግድብ ሰበብ ገንዘብ ሊያፍስ በሄደበት ነው የእህቶቻችን ቁጣ የገነፈለው።

በሴቶች ላይ የሚደርሰው ግፍ በዝቶ ገደቡን ሲጥስ የሚያስነሳው ማዕበል ማንም አያቆመውም። የሰሜን አፍሪቃና የመካከለኛው ምሥራቅ አብዮቶችን በአንክሮ የተከታተለ ማንኛውም ሰው ከሚገረምባቸው ነገሮች አንዱ ሴቶች ያሳዩት ቆራጥነትና እልህ ነው።

በቱኒዚያ የወጣቶች እንቅስቃሴ ውስጥ ወጣት ሴቶች ከመጀመሪያው ጀምሮ የአመራር ቦታ በመያዝ ተሳትፈዋል። በግብጽም የወጣት ሴቶች እልህ ከወንዶቹ በልጦ ታይቷል። ዜጎቿ በኑሮ ደረጃ፣ በባህልም በትምህርትም ከሌሎች ባነሰ ደረጃ ላይ ይገኛሉ በሚባለው የመን ውስጥም ቢሆን የሴቶች ተሳትፎ እጅግ አስገራሚ ነው። በእነዚህ አገራት በተደረጉ ሕዝባዊ ሰልፎች የበርካታ ህፃናትና አረጋዊያን መገኘት በአብዛኛው የሴቶች የተሳካ የቅስቀሳ ውጤት ነው።

የሴቶች ቆርጦ መነሳት በርካታ ቁጥር ያለው ሰው ከማሰለፍ ባሻገር ሌሎችም ተጨማሪ እሴቶች አሉት።

1. ሴቶች ከወንዶች በላይ ታጋሾች ናቸው፤ ሲያመሩ ግን በቀላሉ አይመለሱም። እናም የሴቶች በተቃውሞ ትግል ውስጥ በብዛት መሳተፍ ሥርዓቱ በሕዝቡ ምን ያህል እንደተጠላ አመላካች ነው።
2. የወጣት ሴቶች በድፍረት ለተቃውሞ አደባባይ መውጣት ወጣት ወንዶችን ያጀግናል። የወጣት ወንዶች መጀገን ደግሞ ወጣት ሴቶቹን ይበልጥ ያጀግናል። ወጣት ሴቶችና ወንዶች በእርስ በርስ አርዓያነት ይጀጋገናሉ።
3. የእናቶች መቁረጥ አባቶችን ያነሳሳል፤ የእናትም የአባትም መነሳት ደግሞ መላው ቤተሰብ በሥርዓቱ ላይ እንዲነሳ ያደርገዋል።
4. የሴቶች በትግል አመራር ቦታ ላይ መገኘት በተቃዋሚዎች መካከል ኅብረትን፣ መተሳሰብን በአጠቃላይም ቤተሰባዊ ስሜት ይፈጥራል።
5. ሴቶችና ወንዶች በእኩል የተሳተፉበት ትግል ድል የማድረግ እድሉ ከፍተኛ ነው። ማንኛውም ወገን የመሸነፍን እፍረት መሸከም አይፈልግም!!!
6. ሴቶችና ወንዶች አብረው ሲቆሙ ነው የኅብረት ጥቅም በጉልህ የሚታየው!

ከዚህ አንፃር ስናየው ሰሞኑን በአረብ ኤምሬት ውስጥ የመለስ ዜናዊ አሽከሮች በጠሩት ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች ያሳዩት ቁጭትና እልህ ተስፋ ሰጭ ክንውን ነው።

በዚህ ስብሰባ ውስጥ አንዲት ወጣት "የኢትዮጵያ ባንዲራ የታለ?" ስትል ጠይቃለች። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የአገራችንና የማንነታችን ክብር መገለጫ ነው። ወጣቷ በአለችበት አገር ውስጥ ኢትዮጵያዊያን ክብር ማጣታቸው፤ ኢትዮጵያዊያን ሲሞቱ እንኳን እንደሃይማኖታቸው በክብር የመቀበር ወግ የሌላቸው መሆኑን ከሰንደቅ ዓላማ ክብር መዋረድ ጋር ማመሳሰሏ ልብ የሚነካ ንጽጽር ነው። "የመጨረሻ መሮኛል፣ መሮኛል፣ መሮኛል!!!" በሚሉ ኃይለ ቃላት ንግግሯን መጨረሷ ደግሞ ተስፋ ሰጭ ነው።

እህቶቻችን ከመረራቸው የድላችን ጊዜ ቀርቧል ማለት ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ "በሴቶች ላይ የሚደርሰው ግፍ በሰብዓዊ መብቶች ላይ የሚደርስ ግፍ አካል ነው" ብሎ አድበስብሶ አያልፍም። በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት የሰብዓዊ መብቶች መረገጥ ማነኛው ማሳያ ነው። ይህን ጥቃት መታገል የሴቶች ወይም የወንዶች ኃላፊነት ሳይሆን የሁላችንም ኃላፊነት ነው።

በተጨማሪም ሴቶችና ወንዶች በጋራ ካልታገልን በስተቀር ትግላችንን ፈቀቅ ማድረግ እንደማንችል ግንቦት 7 ያምናል። ስለሆነም "እህቶችና እናቶች በትግላችን በንቃት ተሳተፉ፤ አብረን ታግለን ነፃነታችንን እናረጋግጥ፤ ሁላችን እንደ ዱባይዋ እህታችን 'የመጨረሻ መሮኛል፣ መሮኛል፣ መሮኛል!!!' ብለን ቆርጠን እንነሳ" ይላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

.................................................................................................................................................................................................................

## በጀኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው ኦነግ የወሰደውን . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

ሁሉም የአገራችን ሃይሎች አንድ ላይ ሆነው የህዝባችንን ስቃይና መከራ እድሜ ለማሳጠር በጋራ እንዲታገሉ ዘወትር የሚወተውተው ግንቦት 7 በዚህ መግለጫው፤ ምንም እንኳ የኦሮሞ ሃይሎችን አንድ ላይ ለማምጣት እስከዛሬ የተደረጉ ጥረቶች ለጊዜው ባይሳኩም በአጭር ጊዜ ይሳካ ዘንድ ሁሉም ወገን አቅም የፈቀደለትን ሁሉ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል የሚል እምነት እንዳለው ገልጾአል።

ጥምረት ለነጻነት፤ ለፍትህና ለ እኩልነትም በበኩሉ፤ በጀኔራል ከማል ገልቹ የሚመራው የኦነግ ቡድን ከሌሎች የዲሞክራሲ ሃይሎች ጋር ተባብሮ በአገራችን ውስጥ የተንሰራፋውን ኢፍትሃዊነት ታግሎ ለማስወገድ የሚያስችለውን ይህንን ደፋር እርማጃ በመውሰዱ የተሰማውን ደስታና አድናቆት ገልጾ፤ በአገራችንንና በህዝባችን ላይ እየተፈጸመ ያለውን ሰቆቃ እድሜ ለማሳጠር የሚሹ ሌሎች የኦነግ ሃይሎችም ተመሳሳይ እርምጃ ወስደው የዲሞክራሲ ትግሉን ያጠናክራሉ ብሎ እንደሚያምን አስታውቆአል።

## በኢትዮጵያ የሚገኙ ባንኮች ደንበኞቻቸው ከ200 ሺ ወይም ከ10 ሺ ዶላር በላይ . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መላክ አለበት በሚል መመሪያ መቆጣጠር ይቻላል ብለው ይህንን ውሳኔ እንዲተላልፍ እንዳስደረጉ ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘ መረጃ አመልክቶአል።

አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የባንክ ሰራተኛ ለኢሳት እንደገለጹት ውሳኔው በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በአገር ውስጥ ላሉ የፖለቲካ ሀይሎች የገንዘብ ድጋፍ እንዳያደርጉ ጭምር ለመከላከል ነው ተብሎአል።

ወያኔ በቅርቡ አኬልዳማ በሚል ርእስ በሰራው ድራማ ላይ በውጭ የሚገኙ ሀይሎች በኢትዮጵያ ውስጥ አብዮት ለማስነሳት ከ500 ሺ ብር በላይ መድበዋል በማለት መግለጡ ይታወሳል።
አዲሱ የወያኔ መመሪያ ባለሥልጣናቱ የግለሰቦችን የገንዘብ ሚስጢር ለማወቅ ከፍተኛ እድል ስለሚሰጣቸው በኢትዮጵያ ባንኮች የሚጠቀሙ ዜጎች ችግር ይገጥማቸዋል ተብሎ ተፈርቷል። የጸረሽብር መርጃ ማዕከል ማን ምን ያክል ገንዘብ በየቀኑ እንደሚያንቀሳቀስ በሚደርሰው መረጃ መሰረት የመንግስት ደጋፊ ያልሆኑ ወይም በተቃዋሚነት የተፈረጁ ግለሰቦችን ገንዘብ ለመውረስም ሆነ ጥቃት ሊፈጽምባቸው እንደሚችል ስጋታቸውን የሚገልጹ የፖለቲካ ተንታኞች አሉ።

በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ በተካሄዱ ህዝባዊ አመጾች ስጋት ውስጥ የገባው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ዜጎችን በማሸበርና በፍርሃት በማሸማቀቅ የሥልጣን እድሜውን የሚይራዝም መስሎት የተለያዩ የአፈና እርምጃዎችን እየወሰደ እንደሚገኝ ይታወቃል።

## ሃሰትን እንድናገር ያስገደደኝ መንግስት ነው ማለት አያዋጣም!!!

በዘረኛው ቡድን አማካኝነት የአገራችን የሞራል እሴቶች ሆን ተብለው እየተዋረዱ ነው።ድሮ ድሮ “እውነትን ተናግሮ ከመሸበት ማደር” የሚባል መልካም አባባል ነበረን። ዛሬ ይህን የመሰሉ አባባሎች ከል እንዲለብሱ በመደረጉ እውነትን  የሚናገር በግዞት ተይዞ የመከራ እንጀራ ይበላል የመከራ ውሃም ይጠጣል።

እንደ ንጉስ አክዓብ በዙሪያው ብዙ ሃሰተኛ መማክርትን የሰበሰበው መለስ ዜናዊ የእውነትን ድምጽ የመስማት ልምድ የለውም።ሃሰት የኑሮው መሠረት ነች። ሃሰት አገርን እንደሚሰብር መለስ ጠፍቶት አይደለም በሃስት መሰረት ላይ መቆምን የመረጠው ይልቁንስ አገሪቷን ፈጽሞ ለመሰባበር ካለው እምነት የተነሳ እንጂ። መለስ ዜናዊ የተጠራበት በእውነትና በጽድቅ ላይ የቆመችን አገር ለመፍጠር ሳይሆን በሃሰት ላይ የታነጸች መሠረቷ የሚናወጥ አገርን መፍጠር ነው። መለስ የተጠራበትን ምግባር የቆመለትን ዓላማ እያስፈጸመ በመሆኑ የእርሱ ውሸታምነት አይደንቀንም። እኛን የሚደንቀን የመለስ ዜናዊን ውሸት ለማስፈጸም የሚሽቀዳደሙ ምናምንቴ ግለሰቦች እንደ አሸን መፍላታቸው ነው።

አንዳንዶች ምን እናድርግ ተገደን ወይም ፈርተን ነው እውነት ያልሆነውን የምንናገረው ሲሉ ይደመጣሉ። እውነቱ ግን እውነት ያልሆነውን አለመናገር እምቢ ማለት ሲችሉ ሃሰትን ለመምረጥ ፈቃደኛ መሆናቸው ነው። ሃሰትን አልናገርም፤ ያላየሁትንም አልመሰክርም ለማለት ሰው መሆናቸው ብቻ ያስገድዳቸው ነበር። ሃይማኖታቸው እና ሂሊናቸውም ከእውነት ጋር ብቻ እንዲተባበሩ ይመራቸው ነበር። እነዚህ ግን የውሸትን መንገድ መርጠዋል።ውሸትን በመናገራቸው ዛሬ ሆዳቸውን ሞልተው ለማደር ችለዋል። እንዲህ ያሉቱ ያልሆነውን ሆኗል፤ ያልሰሙትን ሰምተናል፤ ያላዩትን አይተናል ባሉ ቁጥር ብዙ ንጹሃን ዜጎች ለመከራ እንደሚዳረጉ ለማወቅ የሚያንሱ አልነበሩም። ግና ምን ያደርጋል ልባቸው በእግዚአብሄር እምነት ያልጸና፤ሂሊናቸውም በሆዳቸው የተሸነፈ በመሆኑ ከሃሰተኞች ጋር መተባበርን ሙያ አድርገውታል። ይህን ነውራቸውንም “ስማርት” አካሄድ እያሉ ይሞከሻሹበታል። እነርሱ “ስማርት” አካሄድ የሚሉት ነውር ምግባራቸው በወገኖቻቸው ላይ የተፈጸመ ክህደት መሆኑን አበክረን ለማሳወቅ እንወዳለን።

በማንኛውም መንገድ በሃሰት ወገንን ለሚከሱ ቡድኖች የሃሰት መስካሪ ሁኖ መገኘትና ዜጎችን ለመከራ መዳረግ ተቀባይነት ያለው ተግባር አይደለም።ሆድን ለመሙላት ብሎ ያላዩትን እንዳዩ፤ ያልሰሙትን እንደሰሙ አድርጎ  መናገር የሃሰት አባት ለሆነው መለስ ዜናዊ ጀሌና ደጀን መሆኑን እያንዳንዱ ሃሰተኛ ሊረዳው ይገባል። መለስ ሳይፈለግ ሃያ ዓመት በሙሉ በአገራችን ጫንቃ ላይ የተጫነ ጨካኝ ገዢ ነው። ይህን ዘረኛና ዘራፊ ግለሰብ እየዋሹ ለመርዳት መሞከር እውነትን መግደል ሃሰትን ማንገስ ነው።ይህ ደግሞ ከሥነምግባር አኳያ የሰውን ክብርና ማንነት የሚያሳንስ ተግባር ብቻ ሳይሆን እውነት እራሷን ገልጻ ለፈራጅነት እድል በምታገኝበት የታሪክ ምዕራፍ ላይ በወነጀለኝነት የሚያስጠይቅ ነው። በፈረሃ እግዘአብሄር ለሚኖር የእምነት ሰው ደግሞ ወንጀሉ እላይ እሰማይ ቤት ድረስ የሚዘልቅ እንደሆነ የእምነት መጽሃፍትና አባቶች ያስተምራሉ። በምድራችን ህግ ሳይቀር ነውር ከሆነው የሃሰት ምስክርነት ተግባር ውስጥ አለመዘፈቅ እየተቻለ በዚህ ወይም በዚያ ተገድጄ መለስ ዜናዊ በተቀነባበረ የሃሰት ክስ በዜጎች ላይ ለሚፈጽመው ሰቆቃ መሳሪያ ሆንኩ  ማለት በምንም መልኩ ተቀባይነት ያለውና ይቅርታ ሊያሰጥ የሚችል ተግባር አይሆንም።

ክፉውን እንድሠራ ከሚያስገድዱኝ ሃይሎች የሚያድነኝ ማን ነው? አይባልም። የእምነት ሰዎች ከሆንን ከክፉ ጋር እንዳንተባበር የሚያግደን የእግዚአብሄር መንፈስ አለ። ከእምነት ውጪ ከሆን ደግሞ ሂሊና የሚባል የስብዕናችን ምሶሶ አለ። ከዚያም አለፍ ብሎ "ሰው ምን ይለኛል የሚባል" በማህበረሰባችን ውስጥ ከትውልድ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ "ይሉኝታ" አለ።እነዚህን ሁሉ አልፎ እውነትን ከል አልብሶ ሃስተን አስጊጦ መናገር ራሱን ሰው ነኝ ብሎ ከሚቆጥር አካል የሚጠበቅ ተግባር አይደለም።

በአገራችን የነጻነት ጎህ የሚቀድበት ዘመን ሩቅ አይደለም። አሁን የጨለመ የሚመስለው ሊነጋ ሲል እንደሆነም መገንዘብ ያስፈልጋል።እነመለስ በዚያች አገር እንዳላጋጡ የሚቆዩ አይደሉም። እጅግ ሲፈራ የነበረው ጋዳፊ ዛሬ የለም። በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ “እንደ ጋዳፊ አይቀርልህም” እያሉ ወጣቶች መጮሃቸውንም ልብ ማለት ያስፈልጋል። ሃስት እድሜው አጭር ነው። የሃሰት አባት የሆነው መለስ ዜናዊና ቡድኑም እድሜያቸው ረዥም አይደለም። እነዝህን በክፋታቸው ጸንተው ለመኖር የሚመኙትን ቡድኖች ታግሎ ከአገሪቷ ጫንቃ ላይ ማባረር የእያንዳንዱ ዜጋ ግዴታ ነው።ለእነመለስ ውሸት እምቢ ማለት ትክክለኛና የሚያስመሰግን ተግባር ነው። እነርሱ የሚፈጽሙትን ዝሪፊያ መቃወም፤ በዘረኝነት ላይ በተመሰረተ መዋቅር "ከወርቅ ተገኘን" ያሉን የአገሪቷን የፖለቲካ ሥልጣንና የኢኮኖሚ ዘርፎችን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረው በገዛ ሃገራችን ባይተዋር ሲያደርጉን እምቢኝ ማለት ለራሱ ተፈጥሮአዊ ማንነት ክብር ከሚሰጥ እያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ነው።

ድርጅታችን ግንቦት ሰባት የፍትህ፤ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ አገራችንን ከል አልብሶ ሊያዋርዳት ቆርጦ የተነሳውን ዘረኛውን የትግራይ ገዢ ጉጅሌ በመፋለም ለሁላችንም እኩል የሆነች አገር ለመመሥረት የሚችለውን ሁሉ እያደረገ ነው። አገራችን መለስና ቡድኑ ከፈጠሩት ሕፀፅ እንድትፀዳ ቀንና ማታ እየሰራ ነው። ሁሉንም የሚያስኬዱ መንገዶች እየሄደበት ነው። እኛ እንደ ግንቦት 7 አንግበን የተነሳነውን አላማና ግብ ለማሳካት በዘረጋናቸው መንገዶች ሁሉ ተጉዘን መለስና ግብረአበሮቹ ያሰፈኑትን ፍርሃትና ሽብር በመናድ፤ ፍትህና እኩልነት የነገሰባት፤ የሰው ልጆች በነጻነትና በደስታ የሚኖሩባት፤ የበለጸገችና ሉአላዊነቷ የተጠበቀ አገር ለመመሥረት የሚያስፈልገውን መሰዋዕትነት በቁርጠኝነት ለመክፈል ስንዘጋጅ እያንዳንዱ ዜጋ ባለበት ሆኖ አቅምና ጉልበቱ የፈቀደውን ሁሉ ለዚህ የነጻነት ትግል እገዛ ያውላል የሚል እምነት ይዘን ነው።

የግንቦት 7 ድምጽ ዝግጅት ክፍል ዘረኛው መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ በወገኖቻችን ላይ እየፈጸሙ ያለውን ሰቆቃ ለማስቆም በብሄር፤ በቋንቋ፤ በሃይማኖት ወይም በፖለቲካ ልዩነት ሳንከፋፈል ሁላችንም በጋራ መነሳት ያለብን ጊዜው አሁን መሆኑን አብክሮ ያሳስባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

---

## ወያኔ አኬልዳማ በሚል ርዕስ ያስተላለፈው ድራማ ከተቃዋሚ ፓርቲዎችና ከፕሬሶች . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

አቶ ግርማ አያይዘውም፡- “እኛ በምንከፍለው ግብርና ታክስ ጭምር ነው ደመወዝ የሚከፈላችሁ። ሃሳባችን መደመጥ ነበረበት። ሌላው ቀርቶ በምንድነው ቅር የተሰኛችሁት ብሎ የጠየቀን የለም’’ ሲሉ በምሬት ተናግረዋል።

አኬልዳማ ሲሰራ የሕግ አማካሪ አማክረናል የተባለው እንዳልተዋጠላቸው የተናገሩት አቶ ግርማ፤ በፍ/ቤት ተከስሰን ነበር የተባለውም  የአቶ ዘርዓይ ቅሬታ ስህተት እንደሆነ አመልከተዋል።

በሽብርተኝነት ተከሰው ወህኒ በመማቀቅ ላይ የሚገኙት ንጹሃን ዜጎች በቴሌቪዥን ስማችን ጠፍቷል፣ በፍ/ቤት በተያዘ ጉዳይ ላይ ዘገባ መተላለፉ ተፅዕኖ ያሳርፋል በማለት ጉዳዩን እያስቻለ ላለው የወያኔ ፍ/ቤት አቤቱታ ከማቅረባቸው ውጪ በፓርቲው የቀረበ ክስ እንደሌለ የተናገሩት ግርማ ሰይፉ ወያኔ እራሱ ህግ አውጪ እራሱ ህግ ተርጓሚና አስፈጻሚ በሆነበት ስብስብ ውስጥ ምንም ለውጥ ለማምጣት የሚችል ድምጽ እንደሌላቸው ይታወቃል።

በተያያዘ ዜና የወያኔ ራዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ከቴሌቪዥን ባለቤትነት ፈቃድ በዓመት 50 ብር ለመሰብሰብ አቅዶ ቢንቀሳቀስም ፤ውጤቱ ደካማ መሆኑን በረከት በሪፖርቱ ጠቅሶአል።

እንደ በረከት ገለፃ፤ በገቢ አሰባሰቡ ላይ ከቴሌቪዥን ባለቤትነት ፈቃድ ክፍያ የተሰበሰበው ገቢ ለመሰብሰብ ከታቀደው ጋር ሲነፃፀር፤ 26 በመቶ ያህል ብቻ ነው።” ለዚህ ገቢ ማነስ ምክንያቱ የህዝብ ለመክፈል ዝግጁነትና ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን አንዱ ነው ያለው ዋሾው በረከት ድርጅቱም ቢሆን ሕዝቡን በመቀስቀስና በማነሳሳት እንዲከፍል ለማድረግ የሰራው ሥራ ደካማ መሆን ተጨማሪ ምክንያት ነው ብሎአል።

የወያኔ ሬዲዮና ቴለቪዥን ድርጅት  ዳይሬክተር ዘርዓይ በዚህ ረገድ ከፍተኛ ችግር እንዳለ አልሸሸገም “በዓለም አቀፍ ደረጃ አነሰተኛ ክፍያ የምትጠይቅ አገር ኢትዮጵያ ናት፤ በቀን የምናስከፍለው 15 ሳንቲም ነው፤ ብዙ ሰዎች ለአንድ ፊልም ብቻ  30 እና 40 ብር እንደሚከፍሉ እናውቃለን። በኬንያ እና በጅቡቲ ክፍያው በብዙ ዶላር ነው’’ ብሎአል።

ኬንያ የግሎችን ጨምሮ መንግስትን አጠንክረው  የሚተቹና የሚነቅፉ በትንሹ ከ 34 በላይ ልዩ ልዩ ቻነሎች  በነፃነት የሚተላለፉባት አገር መሆኗ እየታወቀ በወያኔ ቁጥጥር ሥር ያለው ባለ አንድ ቻናል ቴሌቪዥን ርካሽና ህዝብ ያሰለቸ የአንድ ፓርቲ ፕሮፖጋንዳ የሚሰራጭበትን የቴሌቪዥን ጣቢያ- ከኬንያ ጋር ለማነፃፀር መሞከር አስቂኝ ነው የሚሉ በርካቶች ናቸው።

ህዝብ የወያኔ ጠባብና ርካሽ የሆኔ ፕሮፖጋንዳ በነጋ በጠባ የሚለፈፍበት ቴለቪዥን ጣቢያ ዋጋ ከፍሎ ለማየት አለመፈለጉ የሚደገፍና የሚበረታታ ነው። አብዛኛው ህዝብ ዲሽ በማስገባት ዓረብ ሳትንና ሎሎች ጣቢያዎችን ወደመከታተል ለመሄድ በመገደዱ በወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ያለው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በተመልካች ድርቀት እንደተመታ መረጃዎች ያሳያሉ።

ዲሽ ለማስገባት አቅማቸው ባለመቻሉ አልፎ አልፎም ቢሆን ኢቲቪን ለማየት የተገደዱትና ”ዲሺ የሌላችሁ፤እንደምን አመሻችሁ” የተባለላቸው ወገኖች ደግሞ እንኳን ግብር ሊከፍሉ ቀርቶ- እኛ ላየንበት ኢቲቪ ሊከፍለን ይገባል በማለት በተደጋጋሚ በኢቲቪ ፕሮፓጋንዳ መማረራቸውን ሲገልጹ ይደመጣሉ።

## የቀድሞ ህወሃት መስራች የነበሩና በአሁኑ ወቅት ደግሞ የመድረክ ፓርቲ አባል የሆነው የአረና ፓርቲ አመራር አቶ አስገደ ገ/ሥላሴ ከመንገድ ላይ ተይዘው ፍርድ ቤት ቀረቡ

አቶ አስገደ ከፍርድ ቤት ሆነው በስልክ ለፍትህ ጋዜጣ እንደገለፁት ከሆነ፣ ከሳሻቸው የቀድሞው የሕወሓት አባል የሆነው ብስራት አማረ ሲሆን ጉዳዩን የያዙት ዳኛ ደግሞ የቀድሞዋ የህወሓት ታጋይ ኪዳን አብርሃ ናት ተብሎአል።

ክስ የቀረበባቸውም ከዚህ ቀደም በፃፉት "ጋህዲ" በተሰኘው መፀሀፍ እንደሆነ አቶ አስገደ ተናግረዋል፡፡

አቶ አስገደ ከአሁን በፊት በዚህ ጉዳይ ቀዳማዊ ወያኔ ፍርድ ቤት ቀርበው ክሱ ተዘግቶ የተሰናበቱ ቢሆንም፤ ሰሞኑን ከመንገድ ላይ መጠሪያ በያዘ ፖሊስ ተይዘው በመቀሌ ከተማ ሰሜን ወረዳ ፍርድ ቤት ቀርበው በስምንት ሺህ ብር ዋስትና ተለቀው ለጥር 2 ቀን 2004ዓም ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ ተቀጥረዋል።

አቶ አስገደ በህወሀት ላይ ጠንካራ ትችቶችን በመሰንዘር ይታወቃሉ።

## ወያኔ በሙስሊም ሃይማኖት ውስጥ እያደረገ ካለው ጣልቃ ገብነት አለመታቀቡ ምዕመናኑን ማስቆጣቱን ቀጥሎአል

ህዝብን በዘርና በሃይማኖት ከፋፍሎ መግዛት ብቸኛ የህይወት እስትንፋሱ የሆነው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ፤ ቀደም ሲል በአገራችን ሙስሉም ህብረተሰብ ዘንድ ፈጽሞ የማይታወቅ አህባሽ የተባለ የእምነት ትምህርት በሃይል ለማስፋፋት እያደረገ ያለውን ዘመቻ በተለያየ የአገራችን ክፍል የሚኖሩ ሙስሊም ወገኖቻችን እየተቃወሙት መሆኑ እየተዘገበ ነው።

በመለስ ዜናዊ የሚመራው የወያኔ አገዛዝ በሃይል ለማስፋፋት የወሰነውን ይህንን አህባሽ የተባለውን አዲሱን የሙስሊም ትምህረት በመቃወም በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ 3 ቁጥር ማዞሪያ ቶታል እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የሚገኘው የአወሊያ ቁጥር 2 ት/ቤት ተማሪዎች ከትናንት በስቲያ ማክሰኞ በእስላማዊ ምክር ቤት ወይም መጅሊስ ላይ ከፍተኛ ተቃውሞ አሰምተዋል፡፡

ተማሪዎቹ ቀኑን ሙሉ የዋለ ተቃውሞ ሊያሰሙ የቻሉበት ምክንያት፤ መጅሊሱ የአረብኛ መምህሮችን ከትምህርት ቤቱ በማባረሩና፤ በምትኩ በራሳቸው ያሰለጠኗቸውንና የአሕባህሽ ተከታይ የሆኑትን በማሰማራት ተማሪዎቹን ከእስልምና ለማስወጣት በማሰባቸው ነው ተብሎአል።

ዜናውን የዘገበው የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ተማሪዋቹ የአህባሽን አመለካከት ፈጽሞ እንደማይቀበሉት፤ የኢስልምና ጉዳይ የበላይ አካል የሆነው መጅሊስ የቀጥር ግቢውን ዘበኞች ሳይቀር ስልጠና ብሎ የት እንደወሰዳቸው እንደማይታወቅ እንደገለጹለት አስታውቆአል፡፡

የአይን እማኞች እንደሚሉት ተቃውሞ በተቀሰቀሰበት ትምህር ቤት በርካታ የወያኔ ፌደራል ፖሊሶች ተገኝተው ግቢውን በማጠር አንድም ተማሪ ከግቢው እንዳይወጣ እንዳፈኑዋቸውና በአካባቢው ያለው ህብረተሰብ ተቃውሞውን እንዳይመለከት የግቢውን አጥር በጨርቅ ሳይቀር ሸፍነውት እንደነበር ይናገራሉ፡፡

የተቃውሞ ሰልፉን ለማክሸፍ በጊቢው የተገኙት የወያኔ ፈደራል ፖልሲ በርካታ ተማሪዎችን አፍሰው ወደ ፖሊስ ጣቢያ ከወሰዱ በኋላ ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስፈታት በነቂስ ከመውጣት አይመለሱም የሚል ሲጋት በአለቆቻቸው ላይ ስላደረ ከአሁን በኋላ ተመሳሳይ የሆነ ተቃውሞ እንዳይቀሰቅሱ በማስጠንቀቅ እንደፈቱዋቸው ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል።

ኢሳት ከትናንትና ወዲያ ማክሰኞ በ3 ቁጥር ማዞሪያ ተነስቶ የነበረው ተቃውሞ የተቀሰቀሰው ቀደም ብሎ ሰኞ ውንጌት አካባቢ ያለው ዋናው የአወሊያ ግቢ ውስጥ ተማሪዎች አሰምተውት የነበረውን ተቃውሞ ተከትሎ እንደሆነ ዘግቦአል።

## ሶማሊ-ላንድ በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን የተመዘገቡ 20 ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን አስገድዳ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ ማድረጓን ሂዩማን ራይትስ ዎች ገለጠ። ዳግም የዚህ ዓይነት ድርጊት እንዳትፈጽምም ጠይቋል

እንደፈረንጆቹ አቆጣጠር ባለፈው ዲሴምበር 28፤ የሶማሊላንድ አስተዳደር ለመንግስታቱ ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽነር ጽህፈት ቤት ወደ ሶስተኛ አገር የጥገኝነት ጥያቄ እንዲሰጣቸው አመልክተው ጉዳያቸውን እየተከታተሉ ያሉትን 20 ኢትዮጵያውያን በሀይል በማስገደድ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ማድረጉን ሂዩማን ራይትስ ዎች ገልጿል።

ይህ ድርጊት "ስደተኞችን ወደማይፈልጉት፤ለነፃነታቸውና ለህይወታቸው አስጊ ወደሆነ ስፍራ አስደድዶ መመለስ የተከለከለ ነው" የሚለውን ዓለማቀፋን የስደተኞች መብትና ህግጋት የጣሰ መሆኑንም ሂዩማን ራይትስ ዎች አመልክቷል።

የሶማሊ ላንድ የአገር ውስጥ ሚኒስትር በበኩሉ ስደተኞቹ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ መደረጉን ሰሞኑን በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አረጋግጧል።

ስደተኞቹ ወደ ኢትዮጵያ ተገድደው ከመመለሳቸው በፊት "ዋጃሌ" ተብሎ በሚጠራው በኢትዮጵያ የቦርደር ከተማ በሚገኘው የስደተኞች ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ከዓለማቀፍ የሰብዓዊ እርዳታ ሰራተኞች ጋር መገናኘታቸውም ተገልጿል።

የሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪካ ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ዳንኤል በቀለ፡-"ሱማሌ ላንድ የስደተኞችን መሰረታዊ መብቶች ልትጠብቅና ልትንከባከብ እንጂ፤ ልትገስስ አይገባትም"ብለዋል።

አቶ ዳንኤል አክለውም፡-" ስደተኞቹን በማስገደድ እንዲመለሱ ያደረገው አካል በቶሎ መጠየቅ አለበት። የአገሪቱ አስተዳደርም የዚህ ዓይነት ድርጊት እንደማይፈጸምም ሊያረጋግጥና ዋስትና ሊሰጥ ይገባል"ብለዋል።

ሶማሌ ላንድ በሚገኝ የስደተኞች መጠለያ ካምፕ ውስጥ ከሚገኙት ከ 28 ሺህ በላይ ስደተኞች መካከል፤ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ናቸው።

ጎሬቤት አገሮች ማለትም ጁቡቲ፤ ኬንያና ሱዳን የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የሚያደርስባቸውን የአካልና የመንፈስ ስቃያ ሸሽተው ወደ ግዛታቸው የሚገቡትን የኢትዮጵያ ስደተኞች አሳልፈው በመስጠት ወንጀል ተባባሪ መሆናቸው ሲዘገብ መቆየቱ የሚታወስ ነው።

## የህወሃት/ኢሃደግ አባላት በአገዛዙ ላይ ያላቸው ቅሬታ እየተባባሰ መምጣቱ ተዘገበ። መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ በሽብርተኝነት ሥም እያካሄዱት ያለው አፈና ለብዙዎች አልተዋጠላቸውም ተባለ

በርካታ ሥራ አጦችንና የመንግሥት ሠራተኞችን በሥራ ዋስትናና የኑሮ ድጎማ ጥቅማ ጥቅሞች በመደለል የአባላቱን ቁጥር ከ5 ሚሊዮን በላይ ማድረሱን በኩራት የሚናገረው ህወሃት/ኢሃደግ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከአባላቱ ጋር ሆድና ጀርባ እየሆነ መምጣቱን የግንቦት7 መረጃ ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን አስታወቁ።

ትግሪኛ ተናጋሪ የሆኑ የህወሃት አባላትን ጨምሮ በአብዛኛው የኢሃደግ አባል ድርጅቶች ውስጥ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ ለመጣው ቅሬታ ዋናው ምክንያት በመላው አገሪቱ ውስጥ እየተስፋፋ የመጣው የኑሮ ውድነት በአብዛኛው አባላቱ ላይ ከደቀነው ከፍተኛ ችግር በተጨማሪ መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ ነጋ ጠባ የሚለፍፉት የኢኮኖሚ ዕድገት በህዝቡ የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ መንጸባረቅ አለመቻሉ የፈጠረው ተስፋ መቁረጥና በድርጅቱና በአመራሩ ላይ እምነት እንዲጠፋ ማድረጉ እንደሆነ ይነገራል።

ሙስናና ሃብት ዘረፋ በሚካሄድባቸው የሃላፊነት ቦታዎች ላይ የሚመደቡ ጓዶቻቸው በብርሃን ፍጥነት በአጭሩ መክበራቸው እንደማንኛውም ተራ የአገሪቱ ዜጎች እያንገበገባቸው መሆኑን በግልጽ መናገር የጀመሩት አባላት ቁጥር እየጨመረ መጥቶአል ያሉት ምንጮቻችን፤ ድርጅታቸው ኢሃአደግ በሚጠራቸው ስብሰባዎች ላይ መገኘት ያቆሙና ወርሃዊ የአባልነት ግዴታቸውን በጊዜ ላለመክፈል የሚያንገራግሩ ሰዎች ቁጥር ስፍር የለውም ብለዋል።

አያንዳንዱ አባል እርስ በርሱ እንዲሳለላ በማድረግ ለቀልድና ለጫወታ የተሰነዘረ ቃላት ሳይቀር በግምገማ ወቅት አለቆች ፊት እየቀረበ አባላት እንዲተቹበትና እንዲሸማቀቁበት ሲያደርግ የኖረው ኢሃአደግ በለመደውና በዘረጋው የውስጥ ጥብቅ ቁጥጥር ተሰሚነቱን ማረጋገጥ እየተሳነው መጥቶአል እንደመረጃ ምንጮቻችን ዘገባ።

"በመላው አገሪቱ ውስጥ በሰፈነው የኑሮ ውድነትና የአስተዳደር ብልሹነት ተማሮ ለውጥ የሚፈልገውን ህዝብ በፈጠራ ወንጀል በሽብርተኝነት ለመፈረጅ አገዛዙ እያካሄደ ያለው ዘመቻ በኢሃአደግ አባልነታችን እንድናፍርና አንገታችንን እንድነደፋ አድርጎናል" የሚሉት በርካታ አባላቱ በአገዛዙ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ለመግለጽ መደበኛ የሆነ የድርጅት ስብሰባ ላይ መሳተፍ ትተዋል ተብሎአል።

አባዛኛዎቹ የኢህአደግ አባላት በፓርቲያቸው ላይ እምነት እያጡና ተስፋ እየቆረጡ መምጣታቸውን እስከ ማዕከላዊ ኮሚቴ ያለው አመራር በግልጽ አውቆታል ያሉት ምንጮች የኑሮ ውድነቱና የአስተዳደር በደሉ የፈጠረው ጥላቻ ሳይደበዝዝ በጸረሽብርተኝነት ዘመቻ ስም እየወሰደ ባለው እርምጃ መሳቂያ መሳለቂያ የሆነ ተግባሩን ቀድሮ የአባላቱንና የመላውን ህዝብ ልብ መልሶ ለመግዛት እጅግ እንደዘገየ ሳይገነዘብ አንዳልቀረ ይናገራሉ።

ህዝባው አመጽ በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ከፈነዳ መመለሱ ከአቅም በላይ እንደሆነ መለስ ዜናዊ አስቀድሞ አውቆታል የሚሉ የውስጥ ምንጮች በደመ ነፍስ እየተወሰደ ያለው የተጠናከረ አፈና ተስፋመቁረጥ የፈጠረው ውሳኔ እንደሆነ በግልጽ ያመለክታል ብለዋል።

በተያያዘ ዜና በአዲሳ አበባ የሚገኙ ነጋዴዎች ግብር ለመክፈል ከፍተኛ የሆነ የቢሮክራሲ ውጣ ውረድ እየበዛባቸው መሆኑን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው ዜና ገለጸ። ግብር በወቅቱ ካልከፈሉ የሚደርስባቸውን ተጨማሪ ቅጣት ለማስወገድ ወደ መሥሪያ ቤቱ የሚጎርፉ ነጋዴዎችን በተቀላጠፈ አሰራር የሚያስተናግድ በቂ ሰራተኛ በቦታው ባለመኖሩ እስከ 5 ቀን የሚረዝም ወረፋ ይዘው እንደሚንከራተቱ ለማወቅ ተችሎአል።

ነጋዴዎች ከአቅማቸው በላይ ግብር እየተጣለባቸው የሚከፍሉትን በማጣት ድርጅታቸውን ለመዝጋት እየተገደዱ መሆኑ በተደጋጋሚ መዘገቡን የገለጸው ዘጋቢያችን የንግድ ፈቃዳቸውን ለመመለስ ወደ አገር ውስጥ መሥሪያ ቤት የሚመላለሱ ሰዎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ መሆኑን ገልጾአል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>፡- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>፡- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org